# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች



# ሩት: የፍቅር ታሪክ

ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest; Alastair Paterson
ያሻሻለው (አሻሻሎ የጻፈው): Lyn Doerksen
የተተረጎመው: Henok Estifanos
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada

©2021 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ቅድመ አያቶቻችሁን፤ወላጆቻቸውን እና በቤተሰባችሁ ውስጥ ከእናንተ ቀድመው የመጡትን ማግኘት የምትችሉ ከሆነ፤ምን አይነት ሰዎች እንደነበሩ ልትደነቁ ትችላችሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፤ከኢየሱስ ቅድመ አያቶች ውስጥ አንዷ የነበረችው ሩት ናት-ጣዖታትን ስታመልክ የነበረች የሞዓብ ሴት ናት።



የሩት ታሪክ የሚጀምረው ከሳምሶም ጊዜ በኋላ ነው፤የእግዚአብሔር ህዝብ እግዚአብሔርን መታመን እና መታዘዝ ባቆሙበት ጊዜ ነበር፡፡አስከፊ የሆነ ረሃብ ምድሪቱን መቷት ነበር፡፡ረሃብ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁን? ያ ትክክል ነው! ረሃብ ማለት ምንም ፍራፍሬ ወይም አዝዕርት የማይበቅሉበት እንዲሁም እንስሳት አንዳንድ ጊዜም ሰዎች ከረሃብ የተነሳ የሚሞቱበት ጊዜ ነው፡፡



አንድ አቤሜሌክ የተባለ ሰው፤ሚስቱን እና ሁለቱን ልጆቻቸሁን ይዞ ምግብ ለመፈለግ ከቤተልሔም ተነስቶ ሄደ፡፡ሰዎች ጣዖታትን ወደሚያመልኩበት ወደ ሞዓብ ምድር ሄደ፡፡



ነገሮች በሞዓብ
ለአቤሜሌክ እና
ለቤተሰቡ በመልካም አልሄደላቸውም፡፡እርሱም ሞተ፤ከዚያም
ሁሉቱ ልጆቹ ተከታትለው ሞቱ፡፡ ሚስቱ ኑኃሚንም ከልጆቿ
ሁለት ሚስቶች




ጋር ቀረች፤ስማቸውም ሩት እና ዖርፋ ነበር፡፡
ሁለቱም ሴቶች ልጆች ከሞዓብ ነበሩ፡፡

ኑኃሚን አሁን መበለት ናት፤እንግዲህ እግዚአብሔር ምድሪቱን እና ህዝቡን እንደጎበኘ እና እንጀራም እንሰጣቸው በሰማች ጊዜ ወደ ምድሯ ልትመለስ ወሰነች፡፡ ነገር ግን ሁለቱን ሴቶች ምን ያደርጋሉ? ኑኃሚንም በሞዓብ እንዲቆዩ እና እንደገና እንዲያገቡ መከረቻቸው፡፡



ዖርፋ ወደ ቤተሰቧ ተመለሰች፡፡ ነገር ግን ሩት እንቢ አለች፡፡ ይልቅ፤ሩት አማቷን ትታ መቼም እንደማትሄድ ቃል የገባችበትን ግጥም ተናገረች፡፡



የኑኃሚን የቀድሞ ጓደኞች ወደ ቤቷ ወደ ቤተልሄም በመምጣቷ በጣም ተደሰቱ፡፡ነገር ግን ኑኃሚን (ደስታ) ብለው ከሚጠሯት "ማራ" (ምሬት) ብለው እንዲጠሯት ለመነች፡፡ "ሁሉንም የሚችል አምላክ አስጨንቆኛልና" ኑኃሚን-ከሩት በስተቀር ምንም ሳትይዝ ተመለሰች፡፡





ሩት በሞዓብ እንዳሉት አብዛኞቹ ሰዎች
ጣዖታትን የምታመል የነበረ
ቢሆንም፤ህያው የሆነውን የእስራኤልን
አምላክ ወደ ማምለክ ተመለሰች። ሩት
የምትመገበው በቂ ምግብ እንዳላት
ለማረጋገጥ ጠንክራ ትሰራ ነበር።
ሁልጊዜ ከአጫጆችም በኋላ
እየተከተለች በእርሻ ውስጥ
የሚወድቀውን ትቃርም ነበር።







የእርሻው አለቃ የሆነው ቦዔዝ ሩት ለአማቷ ምን ያህል መልካም እንደሆነች ሰማ፡፡ ባገኛት ጊዜ፤ቦዔዝ አጫጆቹ ሆን ብለው ከነዶው እያስቀሩ እንዲተዉላት በማዘዝ ረዳት፡፡ ቦዔዝም ሩትን መውደድ ጀመረ፡፡



ሩት ስለ ቦዔዝ እና ደግነቱ
ለኑኃሚን በነገረቻት ጊዜ፤አሮጌቷ ሴት
እግዚአብሔርን አመሰገነች፡፡ "ሰውዬው
ዘመዳችን ነው፤ከቅርብ ዘመዳችን
አንዱ ነው" አለች፡፡





ከብዙ ጊዜ በኋላ፤ቦዔዝ ሩትን ማግባት እና
የኑኃሚን ቤተሰብን መሬት መቤዠት ፈለገ፡፡ነገር
ግን ሌላ የቅርብ ዘመድ የሆነ የመጀመሪያ እድል
ነበረው፡፡ ይህ ሰው መሬቱን ፈለገ- ነገር ግን ሩት
ሚስቱ ትሆን ዘንድ አልወደደም፡፡በህጉ መሰረት
እንዱን ወስዶ ሌላውን አለመውሰድ አይችልምና፡፡

በነዚያ ቀናት፤ሰዎች ስምምነት ላይ ለመድረስ እጆችን አይጨባበጡም ነበር፡፡ ቦዔዝ ጫማውን አውልቆ በህዝብ ፊት ለሌላኛው ሰው ሰጠው፡፡ስምምነቱ ተፈጸመ፡፡ ሩትም ሚስቱ ሆነች፡፡አሁን ሩት እና ኑኃሚን የቦዔዝ ቤተሰብ አባል ሆነዋል፡፡





ቦዔዝ እና ሩት
የመጀመሪያ ልጃቸውን
ኢዮቤድ ብለው
ጠሩት።እርሱም የታላቁ
የአስራኤል ንጉስ የዳዊት
አያት ነው፡፡

ነገር ግን በሚያስደንቅ ሁኔታ፤ህጻኑ ኢዮቤድ የኢየሱስ ክርስቶስ ዘር ግንድ ነው፡፡ኢየሱስ የነገስታት ንጉስ የዓለም አዳኝ ይሆን ዘንድ የመጣው ከዳዊት ዘር ግንድ ነው፡፡



ሩት: የፍቅር ታሪክ

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

ሩት

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት 119:130**

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16